# *የሚሰሩትን ብቻ ከማድነቅ*

# *ራሳችንን ለመስራት እንነቃነቅ*

በአገራችን ውስጥ በመንሰራፋት ያለዉን በጥላቻ የቦካ ፀረ ፌዴራላዊ ስርዐት አራማጀች በመቃወም በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን የአቁዋም መግለጫ በማውጣት ብቻ ዌብ ሳይትና ፌስ ቡክ ከመለጠፍ እንዲሁም በፓል ቶክ ለምላስ መፍቻ ከመጠቀም በዘለለ ምነው እንደ ኢትዮ ሶማል ለፀረ ፌዴራላዊ ስርዓት ና የኢትዮጵያ አንድነት ለማፍረስ ሌት ተቀን በአህዛብ ውስጥ ሰርገው በመግባት የጥላቻ መርዛቸውን በመርጨት የሚገኙትን በመቃወም፤

በተለያዩ ሃገራት የሚኖሩ የኢትዮ ሶማል ማህበረሰብ በተቀናጀ መልኩ ፌዴራላዊት ኢትዮጵያን የሚወክል ባንዴራቸውን በፍቅር ታቅፈው ሃገራችን ለአንድነትዋ ለፈጣኑ ልማትዋ ለማደናቀፍ ከሚሩዋሩዋጡ ሃይሎች አደባባይ በመውጣት ከባድና ጠንካራ ትግል በማድረግ ግንባር ቀደም ኢትዮጵያዊነታቸው እያስመሰከሩ ይገኛሉ።

ስለዚህ እላይ በጠቀስኩዋቸው የአቁዋም መግለጫ ቦታዎች በተጨማሪ ከኢትዮ ሶማል ወገኖቻችን በአጠቃላይ በኢትዮጵያዊነትና በኢትዮጵያ ቀጣይ ህልውናዋን ከምያምን ጋር ተቀናጅተን ስለ የሃገራችን ፌዴራላዊ ስርዓት፣ ሰላማዊና ፈጣን ልማታዊ ግስጋሴዋን ለማስቀጠል አደባባይ ወጥተን በቃችሁ የሚል
ሃገራዊ ግዴታችን መወጣት ይገባናል።

ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የየአገሩ ማህበረሰብ አመራሮች በንቃትና በፍጥነት መንቀሳቀስ ይገባቹሃል።
ይህንን በበጎ ወይም በአንፃሩ የምትመለከቱት ሃሳብ ስጡበት፤ሃሳቡ ለሁሉም ይድረስ፤አስተላልፍ!









